## ‹‹ የስርዓተ-ፆታ አካቶ ትግበራ ››

**ጾታ ምንድን ነው**

ሰዎች ይዘውት የሚወለዱ በወንድና በሴት መካከል ያለ ሥነ- ሕይወታዊ ልዩነትን የሚያሳይ ነው፡፡

**ሥረዓተ-ጾታ ምንድን ነው**

ፆታን መሰረት ያደረገ ስርዓት ማለት ሲሆን በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶችና ወንዶች ያላቸውን ሚና ግንኙነት የሚያመላክት ነው፡፡ ሰዎች ወንድና ሴት ሆነው ከተወለዱ በኋላ እንደማህበረሰቡ አሰራርና አስተሳሰብ ይታነፃሉ፡፡ ይህም ማለት ሴት በሴትነት ወንድ በወንድነት ታንፀው ያድጋሉ ማለት ነው፡፡ ስረአተ ፆታ እንደ ማህበረሰቡ/አካባቢው አስተዳደግ ያሰራር ባህልና ልምድ አኗኗርና የኢኮኖሚ ሁኔታ የወንድና የሴትን ሚና ይወስናሉ፡፡

**ጾታ የተወለዱ ዕለት ይወሰናል ይህም ማለት፡-**

አይለወጥም፣ አለምአቀፋዊ ነው፣ ተፈጥራዊ ነው፣

ሥርዓተ-ጾታ

በኢኮኖሚያዊ፤ማህበራዊ፤ፖለቲካዊ ገጽታዎች ውስጥ የሴቶችንና ወንዶችን ጉዳዩችና ልምዶችን የፖሊሶዎችና የፕሮግራሞች ንድፍ፤ትግበራ፤ክትትልና ግምገማ ዝግጅት ወሳኝ አካል በማድረግ ሴቶችና ወንዶች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑና የሥረዓተ-ጾታ እኩልነት መዛባት እንዳይታይ የሚያደረግ ስትራቴጂ ነው፡፡

ይህ ስትራቴጅ እንደስትራቴጅ የወጣው በ1995 እ.እ.አ በቤጂግ በተካሄዴው 4ተኛው የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ ነው፡፡

ፖሊሲዎች ሴቶችና ወንዶች በእኩል ሁኔታ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና ከውጤቱም እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ነው፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የሥረዓት-ጾታ እኩልነትን በማንኛውም መስክ ለማስፈን የሚያስችል ስትራቴጂ ነው

የሴቶችና የወንዶች ፍላጎት በፖሊሲዎች/ ፕሮግራሞች ዝግጀት፣ትግበራ፣ክትትልና ግምገማ አንድ አካል በማድረግ የሴቶችና ወነዶች እኩል እንዲጠቀሙ እኩል ያለመሆን እድል እንዳይቀጥል የሚያደርግ ሂደት ነው

የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማምጣት ወንዶችና ሴቶች እኩል ኃላፊነት የሚወስዱበትን ሥልት የሚቀይስ ነው

ፖሊሲዎች ሴቶችና ወንዶች በእኩል ሁኔታ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና ከውጤቱም እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥርነው፡፡ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት በአንድ ለሊት የሚመጣ ሳይሆን ሥርዓተ ፆታን በማካተት ሂደት በረዥም ጊዜ የሚደረሰበት ግብ ነው፡፡

ሴቶችና ወንዶች አንድ ዓይነት ፍላጐት እንደሌላቸውና በተለያየ መንገድ መስተናገድ እንዳለባቸው ያምናል ስርዓታዊ ጉዳዮችን የማካተት የመጨረሻ ግብ የስርዓተ ፆታ እኩልነት ማስፈን ነው፡፡

**በባለስልጣኑ ሥርዓተ ፆታን ማካተት ለምን አስፈለገ?**

የሰብአዊ መብት ጉዳይ ስለሆነ

ቀጣይነት ያለውን ልማት እንዲኖር ለማድረግ

ሴቶችን መጥቀም ቤተሰብን መጥቀም ስለሆነ

የሴቶችን ስልታዊ ፍላጐቶች ለማሟላት

ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን

በሀገሪቱ ያሉ ፖሊሲዎች እንደ ጂ.ቲ.ፒ እና ሌሎችም እውን እንዲሆኑ ለማድረግ

**ሥርዓተ-ፆታን የማካተት ስትራቴጂን የሚያሳልጡ ቅድመ-ሁኔታዎች**

የፖለቲካ ቁርጠኝነት (Political Commitment)-የመንግስት አካላት በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ላይ ቁርጠኛ አቋም መያዝን፣ የሕግ ድጋፍና ከለላ መስጠትን፣ የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ በሚያወጧቸው ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግን፣ የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ የሚከታተሉ መዋቅሮችን መዘርጋትና የመሳሰሉትን የፖለቲካ ውሳኔዎች ያጠቃልላል፡፡ተቋማዊ አቅም (Institutional Capacity)-በተቋሙ የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ ለመከታተል ለተዘረጋው መዋቅር ተገቢውን የሰው ኃይል ማሟላት፤ በፋይናንስና በቁሳቁስ መደገፍ፤

በሥርዓተ-ፆታ ግንኙነትና ሚና ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ፤ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ሥርዓተ-ፆታን የማካተት አመራርና አስተዳደር፣ የሴቶች ንቁ ተሳትፎን እና የመሰሰሉትን ሁኔታዎች ያጠቃልላል፡፡

## ተቋማዊ ባህል (Organizational Culture)

ተቋማዊ ባህል በአንድ ተቋም ውስጥ የሥርዓተ ፆታን ጉዳይ አካቶ ለመስራት የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓትና ባህል፣ በፆታና በእድሜ የተለየ መረጃ፣ የዳበረ የሥርዓተ-ፆታ ግንዛቤ፣ ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ልዩ ትኩረት መስጠትና የመሰሰሉትን ሁኔታዎችን ያካትታል፡፡

## ተጠያቂነት (Accountability)

ሥርዓተ-ፆታን የማካተት ስትራቴጂ በአንድ ተቋም ውስጥ በተቀላጠፈ ሁኔታ በስራ ላይ ለማዋል ከሚያስችሉ ሁኔታዎች መካከል አንዱ፣ በተቋማት "የተጠያቂነት" አሰራር መኖር ነው፡፡ ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ሁሉ ተጠያቂ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የአሰራር ስርዓት፣ ስትራቴጂውን ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡

## ሥርዓተ-ፆታ ማካተት ደረጃዎች

በተቋማት ላይ ሥርዓተ-ፆታን የማካተት ስልት በሁለት ጥምር ደረጃዎች ተለይቶ ይተገበራል::

**በተቋም ደረጃ የሥርዓተ-ፆታን ማካተት** በተቋም ደረጃ የሚደረግ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት የሚያተኩረው

-

በተቋሙ አደረጃጀትና ሂደቶች ላይ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ መግባታቸው ላይ ነው፡፡ በተቋም ደረጃ የሚከናወነው ሥርዓተ-ፆታን የማካተት ስልት ትኩረቱ የሚያደርገው በተቋማዊ አደረጃጀት፣ በህግ ማዕቀፎች፣ በሰራተኛ የፆታ ምጥጥን፣ በተቋማዊ ባህል ወዘተ ላይ ይሆናል፡፡

## በፕሮግራምና ፕሮጀክት ደረጃ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት -

በፕሮግራም እና ፕሮጀክት ደረጃ ላይ የሚደረገው የሥርዓተ-ፆታን የማካተት ስልት ትኩረቱ ተቋሙ የተቋቋመበትን ዓላማ ለመተግበር በሚቀርፃቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ ይሆናል፡፡ በተቋሙ የሚቀረጹ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ከዕቅድ እስከ ማጠናቀቅ ሥርዓተ-ፆታን አካታች በማድረግ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እንዲሰፍን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ዓላማ ያደረገ ነው፡፡

## ሥርዓተ ፆታን ማካተት በግብርና ቁጥጥር

ሥርዓተ ፆታን በግብርና ቁጥጥር ስራ ማካተት ማለት ሴቶችንና ወንዶችን በግብርና ቁጥጥር ስራዎች እና በአመራርነት ያላቸውን ተሳትፎ ማሣደግ እና በግብርና የሥራ እንቅስቃሴ ውጤትም ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መፍጠር ማለት ነው፡፡

**በግብርና ቁጥጥር ስራዎች ሴቶችና ወንዶች እንዲሁም ወጣቶች በእኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምን መደረግ አለበት?**

ችግሮችን መለየት የጋራ ግዜቤ መውሰድ

ከእቅድ ጀምሮ ስረዓተ ጾታን ማካተት

የስርዓተ ፆታ ማካተት መመሪያ ማዘጋጀት

ተጠያቂነትን መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

የሴቶች ጉዳይና ማህበራዊ አካቶ ትግበራ ስራ አስፈፃሚ በ2017 በጀት ዓመት ካከናወናቸው በርካታ ስራዎች ውስጥ በዋናነት ሶስት ግቦች ላይ ትኩረት አድርጓል፡ ሴቶች በባለስልጣኑ ውስጥ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ለሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶችና ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎና ጥቅም ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ እንዲሁም የማህበራዊ አካቶ ትግበራ በአካባቢና ማህበረሰብ ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ለመቀነስ ክትትል ማድረግ ናቸው።

ክፍሉ ከሰራቸው በርካታ ስራዎች ውስጥ ለማሳያ ከተገለፁት መካከል፡-

1. የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ
   * በስርዓተ-ፆታ እና ፆታዊ ትንኮሳ መከላከል ዙሪያ 105 ሰራተኞች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡
   * በሁሉም የስራ ክፍሎች የስርአተ ፆታ ማካተት መከታተል
   * ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በተመለከተ ከ104 ሴት ሰራተኞች ጋር ማክበር ተችሏል፡፡
   * ለስራ አስፈጻሚዎችና ቡድን መሪዎች አጠቃላይ 81 ለሚሆኑ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
2. ለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ መስጠት
   * ወላጆቻቸውን ላጡ ህጻናት የገንዘብ ድጋፍ (20,650 ብር) ፣የህጻናት ማቆያ ማዕከል ማቋቋም እና ድጋፍ መስጠት (4 ህጻናት ተጠቃሚ ሆነዋል)፣
   * የሴቶችና ወጣቶች ተክሞሮአቸውን ለማሳደግ ድጋፍ መስጠት (60 ሴት ሰራተኞች ስልጠና አግኝተዋል)
   * በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ኤች.አይ.ቪ ኤድስን እና ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል ዙሪያ ስልጠና መስጠት (148 ሰራተኞች)

3.የአካባቢ ተጽእኖን መከላከል

* አምራች ተቋማት የአካባቢ ተጽእኖ ምዘና ስርዓት መተግበራቸውንና ባህላዊ እሴቶች፣ ቅርሶች እና የሰራተኞች ደህንነት መጠበቃቸውን መከታተል
* የማምረቻ መሳሪያዎች በአካባቢና በአየር ንብረት ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ መገምገም
* የግብርና ግብዓቶች በአካባቢው ጤና ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ክትትል ማድረግ ናቸው፡፡

**በኢትዮጲያ ግብርና ባለስልጣን በህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ የተዘጋጀ**

**ሰኔ 2017 ዓ.ም**